# *ሀሳብ የሌለበት ሂሳብ*

*መስፍን ወልደ ማርያም*

*ሐምሌ 2001*

*‹‹ያለዎት ቀሪ ሒሳብ›› የሚል የአቶ መስፍን ሴኮንዶ ሚስቶ ወይም ጋሬ* (*አዲስ ነገር* 11/11/2001) *አዲስ ነው፤ ከሒሳብ ይነሣና እንደአዋሽ ቁልቁለቱን ወርዶ አሸዋ ውስጥ ይገባል፤ ርዕሱ ሂሳብ ስለሆነ መስመሮቹን ቆጠርኋቸው፤* 183 *ናቸው፤ መጣያው ‹‹በነገራችን ላይ›› የሚለው ከተጨመረ* 195 *ይሆናሉ፤ ከ*195*ቱ* 50 *ያህሉ ስለጸሐፊው ነው፤ ብዙ መስመሮች ደግሞ ትልቁ ስዕል ወይም አገራዊ ስዕል የሚል የቡና ቤት ፍልስፍና ቢጤ ወስዶአል፤ ሌሎች ብዙ መስመሮች ስለሲኖዶሱ ስብሰባ ይነካካሉ፤ የፖሊቲካ ጸሐፊዎች ተግባር አሥራ ሁለት መስመሮች ተችረዋል፤ በርከት ባሉ መስመሮች ስለኢሕአዴግና ‹‹ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች›› በአጠቃላይ ተግሳሣጽና ምክር ቢጤ ተሰጥቷል፤ እስካሁን ግራ ገብቷችሁ ከሆነ የተፈለገውም ያው ሳይሆን አልቀረምና የናንተ ጥፋት አይደለም፤ ጥቂት መስመሮችም በኢሕአዴግ ላይ የተሰነዘረውን ሂስ ለመከላከል ውለዋል።*

*ካልሰለቻችሁና ካልተዋችሁት የተማሪው ፈረስ ታሪክ ላይ ትደርሳላችሁ፤ ፈረሱ ሀ ሁ ሂን ይቆጥርና ሃ ራብዕ ዘንድ ሲደርስ ሀ ግዕዝን ረስቶታል! እንደአንድነት!*

- *ጋዜጠኛ እንደማናችንም የራሱ የሆነ አስተያየት አለው፤ ነገር ግን አስተያየቱን ከሁነቱ ማስቀደም የተግባሩ ሥነ ምግባር አይመስለኝም፤ ‹‹ባለጌ ጽሑፍ›› ይልና ብልግናው ምን እንደሆነ አይናገርም፤ እንዲያውም በዚያ ጽሑፍ ውስጥ ስንቱና የትኞቹ ጉዳዮች በድምፅ ብልጫ የተወሰኑ እንደሆኑ ቢጠየቅ አይመልስም። ከመቶ ዘጠና አምስት መስመሮች ያላነሰ ጽሑፍ እንዲያቀርብ ታዞ ቢሆንም ከዚያው ጽሑፍ ብቻ ሊያገኘው ይችል ነበር፤ የማንበብ ትእግስት ቢኖረው፤*
- *በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የተከሰተውን ችግር ለአንባቢዎቹ ለማስረዳት ሳይሆን አንዱን ወገን ሥራ ፈትና ማሰብ የተሳናቸው በማለት ወደዘለፋም ይገባል፤ እንዲህ ስድም ቢሆን በጋዜጠኛ ነጻነት አምናለሁ። ግን ይህንን ጋሬ መጫጫር ማሰብ ተብሎ እንጀራ የሚያበላ ከሆነ የዕድል ጉዳይ ካልሆነ ሥራ ፈት ለምን ይኖራል? የሚያስደንቀው ግን ዘለፋውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ* 150*ኛው መስመር ላይ ጋዜጠኛነቱ ትዝ ይለውና ‹‹በዚህ ወይም በዚያኛው ጉዳይ ንጹሕ ወይም አጥፊ ናቸው ብሎ ዝርዝሮች ውስጥ መግባት አያስፈልገኝም፤ አያገባኝምም፤›› ይላል! ማሰብ እንዲህ ነው፤ የሚያታልለው አንባቢውን ነው ወይስ ራሱን?*
- *አንድ ተራ የእንግሊዝኛ ሐረግን ወደአማርኛ ተርጉሞ በቅንፍ ውስጥ በማስገባት ትልቅ ፍልስፍና አስመስሎ ለመራቀቅ መሞከር ዋና ጉዳይ ይሆናል ተብሎ ለተፈለገው ምንም ፋይዳ የለውም፤*--(UNITY is THE LARGER PICTURE)
- *‹‹በጥንቃቄ ልጓም ውስጥ›› ሆኖ የሚጽፈው የፖሊቲካ ተንታኝ ጋዜጠኛ በ*104*ኛው መስመር ላይ የሚከተለውን ይላል፤ ‹‹አሁን ጭንቅ የሆነው ለዚህ በአብላጫ ድምፅ ለጸደቀ ውሳኔ ተገዢ ብቻ ሳይሆን ታዛዥም* (*ተገዢ ሆኖ ታዛዥ መሆን አይቻልም ለማለት ይሆን?*) *ሆኖ የመገኘት የዴሞክራሲ መርሕ ነው። ዴሞክራሲን በቃል የሚያንቆላጳጵሷት ሰዎች ለገዛ ፓርቲያቸው ለብዙኃን ውሳኔ መገዛት ያቃታቸው ሆነዋል።›› ቀደም ሲል በ*89*ነኛው መስመር ላይ ስለአንድ ተማሪ ፈረስ ታሪክ ሲናገር ፈረሱ ፊደል መቁጠር ጀመረና ሀ ሁ ሂ ብሎ ሃ ራብዕ ዘንድ ሲደርስ ሀ ግዕዝን ረሳው! አንድነቶችም ከቅንጅት*

የተማሩትን በመርሳታቸው እንደፈረሱ ሆኑ ይላል። ትንሽ ወደእውነት የተጠጋው እዚህ ላይ ነው፤ ግን እሱ ይበልጥ ወደፈረሱ የሚጠጋበትን መንገድ ከፍቷል፤ በአብላጫ ድምፅ መገዛት ‹‹የዴሞክራሲ መርሕ›› ነው ሲል ሀ ሁ ሂን ረስቶ ነው፤ እንደፈረሱ! የድምፅ ብልጫ በእኩልነት፣ የድምፅ ብልጫ በሕጋዊ ሥርዓት፣ የድምፅ ብልጫ በነጻነት፤ እኩልነትን፣ ሕጋዊ ሥርዓትንና ነጻነትን አስወጥቶ፣ ወይም ከሦስቱ አንዱን እንኳን አስወጥቶ የድምፅ ብልጫ ብቻውን የዴሞክራሲ መርህ ነው ማለት ወይ ቁም ነገሩን መርሳት፣ ሲብስም አለማወቅ ነው፤ ማስረጃ ብጠቅስ ለኢሕአዴግ ተቆርቋሪነቱን ገልጾአልና ይናገርብኛል!

- ወደሂሳቡ ስመጣ ብዙ የተረሳ ነገር አለና ሀ ሁ ሂን ሳንረሳ ሃ ራብዕ ላይ ስንደርስ ብንወያይበት ይሻላል።

ጋዜጠኛ መስሎ፣ ርእሱን የሂሳብ እውቀት አንተርሶ፣ አንድ የእንግሊዝኛ ተራ ሐረግን ተርጉሞ ትልቅ ፍልስፍና አስመስሎ፤ የፖሊቲካ ጸሐፊዎችን የአጻጻፍ የጥንቃቄ ልጓም በማውራት የፖሊቲካ አዋቂ መስሎ፣ ስለዴሞክራሲም ከሌሎች ይበልጥ አዋቂ መስሎ እየዘለሬ ለማስተማር የከጀለ ሰውን የገፋፋው ምንድን ነው? ሁሉንም ሲመስሉ አንዱንም መሆን አይቻልም፤ ስለዚህም አንባቢው በግድ ግራ ይገባዋል።

ብልጥ ያልሆነ ሰው ብልጥ ለመሆን ሲጥር ቂል ይሆናል፤ የመራቀቅ ብቃት የሌለው ሰው ለመራቀቅ ሲፍጨረጨር ተራ ይሆናል፤ ዝና እንቅፋት የበዛበት ቀጥ ያለ መንገድ ነው፤ ወለም ዘለም ለሚሉ አይሆንም።

በመጨረሻ አንድ የምወደው የትግርኛ አባባል ልናገር፤--- ዓርባ አምባሻ ከመላስ አንዱን መጉረስ!